**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2018 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 005384**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የቃል መጽሐፍ ቅዱስ

ፍርድና መግቢያ — ለአዲስ ገቢዎች መጠይቅ

## ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሁለት ምዕራፎች ይዟል።

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — (4x16) — | 64 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — (3x12) — | 36 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | — | 100 ነጥብ |

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያ፦ የለም።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።
በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ח, 2018

**מספר השאלון: 005384**

**תרגום לאמהרית (6)**

# תורה שבעל פה

דינים ומבוא — שאלון לעולים חדשים

## הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שעה וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שני פרקים.

| | | |
|---|---|---|
| פרק ראשון | — (16x4) — | 64 נקודות |
| פרק שני | — (12x3) — | 36 נקודות |
| סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי־לועזי / לועזי־עברי.

ד. הוראות מיוחדות: אין.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).
רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አራቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 16 ነጥብ)።

1. የቃል መጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ

ሀ. በ"ጥንዶች ዘመን" ("תקופת הזוגות") በሕዝቡ ላይ ሁለት ጠቢባን በመሪነት ተቀምጠው ነበር። የእያንዳንዳቸውን የሥራ ድርሻ ጥቀስ። (5 ነጥብ)

ለ. (1) የአሞራዊያን ዋና ሥራ (ተግባር) ምን ነበር?

(2) የባቢሎንን ታልሙድ ሁሉም የማህበረሰብ ዘርፎች ሲቀበሉት የኢየሩሳሌምን ታልሙድ ግን ጥቂቶች ተሳትፈውበታል።
ለዚህ እውነታ አንድ ምክንያት ጻፍ።

(8 ነጥብ)

ሐ. א"הרמ ("ሃራማአ") "ሃማፓ" ("המפה") የሚለውን ድርሰት ጽፏል። የዚህ ድርሰት ይዘት ምን ነበር? (3 ነጥብ)

2. ጸሎት

ሀ. ለምንድን ነው ጠዋት "እጅ መታጠብ" (נטילת ידיים) የሚያስፈልገው? ሁለት ምክንያቶችን ጻፍ። (8 ነጥብ)

ለ. (1) ለምንድን ነው ከጸሎት በፊት መዘጋጀት የሚያስፈልገው?

(2) ጸሎትን በልብ ብቻ ማለት የማይቻለው ነገር ግን በቃላት መግለጽ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? አንድ ምክንያት ጻፍ።

(8 ነጥብ)

3. ቡራኬዎች

ሀ. ዕቃ ለ"እጅ መታጠብ" ካሼር ይሆን ዘንድ ሊያሟላቸው የሚገባውን ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ጻፍ። (5 ነጥብ)

ለ. (1) በብርካት ሃማዞን አራት ቡራኬዎች አሉ።
ከቡራኬዎቹ ውስጥ የሁለቱን ሥም ጻፍ እና የጻፍካቸውን ሁለት ቡራኬዎች የእያንዳንዳቸውን ይዘት በአጭር በአጭሩ ዘርዝር።

(2) በሰንበት ቀን እና በበዓላት በብርካት ሃማዞን ላይ ተጨማሪ ቡራኬዎች ይጨምራሉ።
አንድ ጭማሪ ጥቀስ እና የሚጨመረው በሰንበት ወይም በበዓል ቀን እንደሆነ ጻፍ።

(11 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

**4.** ሰንበት

**ኦ.** በሰንበት ቀን ኦሪት ከተነበበ በኋላ "ሃፍታራ" ("הפטרה") ይነበባል።
"ሃፍታራ" ምን እንደሆነ አብራራ። (4 ነጥብ)

**ኀ.** በአዘቦት ቀናት ሦስት ጸሎቶች ይጸለያሉ እና በሰንበት ቀን ተጨማሪ ጸሎት ይጸለያል።
ይህ ጸሎት ምንድን ነው? ለምንስ ነው ጠቢባን ይህን ጸሎት ያስተካከሉት? (6 ነጥብ)

**ኀ.** (1) በሰንበት ቀን ሦስተኛ ማዕድ (סעודה שלישית) የሚበላበት ጊዜ መቼ ነው?
(2) በሰንበት ቀን ሦስተኛው ማዕድ እና በሌሎቹ ማዕዶች መካከል ያለውን አንድ የሐይማኖታዊ ሥርዓት ልዩነት ጻፍ።
(6 ነጥብ)

**5.** ሞአዲም — "ምፃሪም" (በሐዘን ወቅት) ባሉ ቀናት ውስጥ

**ኦ.** (1) በ"ምፃሪም" ባሉ ቀናት ውስጥ የማይደረጉ ሁለት ድርጊቶችን ጻፍ።
(2) በ"ታሙዝ 17 (י"ז בתמוז) የሆነ አንድ ክስተት እና በ"ቲሽዓ በአቭ" (תשעה באב) የሆኑ ሁለት ክስተቶችን ጻፍ።
(10 ነጥብ)

**ኀ.** (1) ከ"ቲሽዓ በአቭ" ስቃዮች (עינויים) ውስጥ አንዱ መብላት እና መጠጣት መከልከሉ ነው።
በ"ቲሽዓ በአቭ" ካሉት ስቃዮች ውስጥ ተጨማሪ ስቃይ ጻፍ።
(2) በ"ቲሽዓ በአቭ" የሚነበበው "መጊላ" የቱ ነው?
(6 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሁለት** (36 ነጥብ)

ከ6-9 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 12 ነጥብ)።

**6.** የተፈቀዱ (ካሽር የሆኑ) ሐይማኖታዊ ትዕዛዛት

**አ.** ዋናው የእስራኤል ራባናት የካሽሩት ክፍል ከሚቆጣጠራቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሥጋ ዘርፍ ነው። በሥጋ ዘርፍ ቁጥጥር የሚያስፈልግበትን አንድ ምክንያት አብራራ። (4 ነጥብ)

**ב.** (1) ሁለት ጥሩ ጓደኛሞች አብረው መብላት ይፈልጋሉ። አንዱ ሥጋ መብላት ይፈልጋል ሌላው ደግሞ የአይብ ኬክ መብላት ይፈልጋል።
ሁለቱም አንድ ጠረጴዛ ዙሪያ መብላት ይችሉ ዘንድ ማድረግ ያለባቸውን አንድ ድርጊት ጻፍ።

(2) ምግብ የሚያዘጋጅ ሰው የሥጋ ሾርባ ቀመሰና ወዲያውኑ ወተት ነክ ምግብ መመገብ ፈለገ። በየትኛው አጋጣሚ ነው አፉን መታጠብ ብቻ በቂ የሚሆነው?

(8 ነጥብ)

**7.** ሞአዲም — "ሽሚኒ አጸሬት" (שמיני עצרת) እና "ሲምሃት ቶራ" (שמחת תורה)

**አ.** (1) "שמיני עצרת" ራሱን የቻለ በዓል እንጂ ከሱኮት በዓል ጋር እንደማይጠቃለል የሚያረጋግጡ ሁለት የሃይማኖት መመሪያዎች ጻፍ።

(2) በእስራኤል አገር ውስጥ "שמיני עצרת" የ"שמחת תורה" በዓልም ነው።
በ"שמחת תורה" ስለ ምንድን ነው የምንደሰተው?

(7 ነጥብ)

**ב.** በሲምሃት ቶራ ሁለት "አማቾች" ("חתנים") ቶራ ሊያነቡ ይወጣሉ።
የእነዚህ "חתנים" የእያንዳንዳቸው መጠሪያ ስም ማን እንደሆነ ጥቀስ እና ከእነሱም እያንዳንዱ በቶራው ውስጥ የትኛውን ክፍል እንደሚያነብ ጻፍ። (5 ነጥብ)

**8.** የአዳር ወር

**አ.** ከ"ארבע הפרשיות" ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ እና ይዘታቸውን በአጭር በአጭሩ አብራራ። (8 ነጥብ)

**ב.** ከፑሪም ትዕዛዛት ውስጥ አንዱ ለድሆች ስጦታ መስጠት ነው።
ስንት ስጦታዎች መስጠት እንደሚያስፈልግ እና እነዚህ ስጦታዎች ለስንት ድሆች እንደሚሰጡ ጻፍ።
(4 ነጥብ)

**9.** ትዕዛዛት (מצוות) — ግርዛት እና የወንድ ልጅ "ፒዲዮን" (ברית מילה ופדיון הבן)

**አ.** (1) ቅዳሜ ማታ የተወለደ ሕጻን – ግርዛቱ በየትኛው ቀን ነው መካሄድ ያለበት? መልስህን አስረዳ።

(2) ወላጆቹ በልጅነቱ ያላስገረዙት ትልቅ ሰው – ምን ማድረግ አለበት?

(6 ነጥብ)

**ב.** የበኩር ወንድ ልጅን መቤዠት (לפדות) ትዕዛዝ።

(1) ይህ ትዕዛዝ የሚፈጸመው ልጁ ከተወለደ ከስንት ቀን በኋላ ነው?

(2) የበኩር ወንድ ልጅ የማይቤዥባቸውን ሁለት ሁኔታዎች ጻፍ።

(6 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך